የኔ አባት.... ሰንበት ትምህርት ቤት ማለት

የኔ አባት ብዙ ጊዜ ሳዮት የሰንበት ትምህርት ቤት ነገር የገባዎት አልመሰለኝም... መቼስ ከርሶ ባላውቅም ጥቂት ልበልዎት.. አደራ ያስተውሉኝ!

ሰንበት ትምህርት ቤት ማለት የኔ አባት... እኛ ልጆችዎ ሰው የሆንበት ሥፍራ ነው። ሰንበት ትምህርት ቤት ማለት የኔ አባት... በፍቅር ወድቀን፣ በፍቅር ተነሥተን፣ በፍቅር ተርበን፣ በፍቅር በልተን፣ በፍቅር ተጣልተን፣ በፍቅር ታርቀን፣ በፍቅር ተኮራርፈን ፣ በፍቅር ተጨዋውተን፣ በፍቅር አልቅሰን፣ በፍቅር ስቀን፣ በፍቅር ኮርኩመን፣ በፍቅር ተኮርኩመን፣ በፍቅር ተፎካክረን፣ በፍቅር ተሸናንፈን፣ በፍቅር ተምረን፣ በፍቅር ተተራርበን፣ በፍቅር አጥፍተን፣ በፍቀር ታርመን እኛነታችን የተሠራበት ቦታ ነው። አባቴ ይሙቱ! ... እኔ በርሶ ምዬ አልዋሽም።

ሰንበት ትምህርት ቤት ማለት የኔ አባት... በፍቅር ባሪያ የሆንበት፣ በፍቅርም ገዢ የሆንበት ቦታ ነው። አሽከርም ንጉሥም ሆንበታል፤ አባቴ አሽከርና ንጉሥ በአንድ ጊዜ ሆነው ያውቃሉ? በፍቅር ባሪያም ገዢም ሆነውስ ያውቃሉ? በእውነት እንደዛ ከሆኑስ እርሶም ሰንበት ተማሪ ኖት ማለት ነው። ነቃሁቦት፤ ሰንበት ትምህርት ቤት ማለት የኔ አባት ልጅ ሳለን ሥራ አመራርን ያጠናንበት፣ የሕዝብ አስተዳደርን የተማርንበት ፣ በተለያየ ሙያ ስብጥር የተሰባጠርንበት፣ ለአረንጓዴ ልማት አትክልትን የተከልንበት፣ በሀገር ፍቅር የነደድንበት፣ በዕቅበተ እምነት የበለጸግንበት፣ በበጎ አድራጎት ስለ ወገን ማሰብን ያየንበት፣ ለሀገር ጥሩ ዜጋ መሆንን የቀሰምንበት ቦታ ነው።

ሰንበት ትምህርት ቤት ማለት የኔ አባት... ካለዘር ክፍፍል የተፋቀርንበት፣ እገሌ ከዚህ ነው እገሌም ከዚያ ነው ያልተባለበት ሰሜንና ደቡብ፣ ምዕራብና ምስራቅ የሌለው ቦታ ነው። ሰንበት ተማሪ ሲሆኑ አባቴ... ብሔሮ ክርስትና፣ ቋንቋዎ ፍቅር ፣ ሀገርዎ በሰማይ ፣ ንጉሦ ክርስቶስ ይሆናል።

እመቤቴን! የኔ አባት... መቼስ ከእርሶ አናውቅም፣ እንደርሶ ሊቅም አይደለንም፣ ብሉዩን ከሐዲሱ ፣ ሊቃውንቱን ከመነኮሳቱም አናመሰጥር ይሆናል፤ ሰንበት ተማሪ ሲኮን ግን አባቴ... በሐዲስ ኪዳንና በብሉይ ኪዳን ያለው እንደ እሳት የሚንቀለቀል ፍቅረ ቤተ ክርስቲያን በውስጥዎ ይነዳል። ቤተ ክርቲያን ስትነካ አካሎ እንደተቆረጠ ያንገበግቦታል፤ ትምህርትዎን ሥራዎን እርግፍ አድርገው መፍትሔ ለመስጠት ይሮጣሉ፤... ብቻ አባቴ ሰንበት ትምህርት ቤት የቅንዐተ ቤተ ክርስቲያን እሳት የሚንቦገቦግባት ምድጃ ናት።

አባቴ... ሰንበት ትምህርት ቤት ማለት፣ እርሶ የሚወዷቸው ትልቁ መምህር የተማሩበት ቦታ ነው፤ እርሶ የሚያከብሯቸው ትልቁ ሊቅም ማስተማርን የጀመሩበት ቦታ ነው፤ ያኔ ተኮለታትፈው ባያስተምሩን ኖሮ ዛሬ እርሶን የመሰለ አባት በተገኙበት ጉባኤ ለማስተማር መንፈሳዊ ልምድ አይኖራቸውም ነበር። እኛ አሜን ባንላቸው ኖሮ ዛሬ በሺ የሚቆጠር ምእመን አሜን አይላቸውም ነበር። ድንግልን! በዚህ ቅንጣት አልጠራጠርም።

ሰንበት ትምህርት ቤት ማለት የኔ አባት... የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች የሆኑ ተኩላዎች እንደጉድ የሚፈሩት ቦታ ነው፤ የቤተ ክርስቲያን የቁርጥ ቀን ልጆች አሉበታ፤ አባቴ... ሰንበት ትምህርት ቤት እንደ ጳውሎስና እንደ ሲላስ ሲያገለግሉ የሚታሠሩበት ቦታ ነው፤ ያኔ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች የእግዚአብሔር ቅዱሳንን ነገር እየጠመዘዙ ከነገሥታት ጋር እንደሚያጣሉና በምድራዊ ፍርድ ቤት እንደሚገትሩ... በሰንበት ትምህርት ቤትም እንዲሁ ነው፤ ለሃይማኖት ሲቆረቆሩ የፖርቲ አባል የመንግሥት ጠላት ተደርገው ይከሰሳሉ፤ የቤተ ክርስቲያንን መዘረፍ ሲቃወሙ በዓለማዊ ፍርድ ቤት አሸብረዋል ተብለው ይገተራሉ።

ሰንበት ትምህርት ቤት ማለት የኔ አባት ወንድምዎ በኃጢአት ሲወድቅ እንደእነ ቅዱስ መቃርዮስ የወንድሞን ነውር ለመሸፈን ቅርጫት የሚደፋበት ቦታም ነው። በየቦታው ሲናቁና ሲባረሩም በፍቅር ተመክረው የሚመለሱበት ገዳም ነው። በወጣትነት ብዙ እያጠፉ በብዙ የሚማሩበት ቦታም ነው።

አባቴ... እውነተኛ ወንድሞች አሉዎት? በሐዘንዎ ጊዜ ሳይለዮት ከልብ የሚያስተዛዝኖት፣ ማስተዛዘን ብቻም ሳይሆን በመንፈስ የሚያጸኑዎት... ወንድሞች አሎት? አብረው ውለው አብረው አድረው... እንግዳን አስተናግደው፣ ዕቃ አጥበው የሚያግዙዎትስ እኅቶች አሉዎት? በደስታዎ ጊዜ ከእርስዎ ጋር አብረው ከልብ የሚደሰቱ፣ ድግሱን ድግሳቸው አድርገው የሚንደፋደፉ ወዳጆች አሉዎት? እኚህ ከሌሉዎት የኔ አባት አንድ ነገር ጎሎታል ማለት ነው... ሰንበት ተማሪነት አልነካካዎትም ማለት ነው።

ሰንበት ትምህርት ቤት ማለት የኔ አባት አንድነትና ኅብረት አካል ነሥቶ የሚያዩበት ቦታ፤ አባቴ ይሙቱ እውነቴን ነው። አንድነትና ንጹህ ፍቅር በስምንተኛው ሺ ገዝፎ የሚታይበት ገነት ነው ሰንበት ትምህርት ቤት። ለዛ ነው እኮ አባቴ... ሰነፍ ሆነን እንኳን እንደ ብርቱ የምንታየው፣ ምንም ሳንደክምበት እንኳን አገልግሎታችንና ሐሳባችን የሚሞላው... ምንም ሳናውቅ እንኳን ከአዋቂዎች በላይ የምናገለግለው... አባቴ ይሙቱ... ይኸው በርሶ ምያለሁ... ይሄ ሁሉ ስለአንድነታችንና ስለፍቅራችን ነው። እንጂማ እኛ እኮ ባዶ ነን...፤ ሰንበት ትምህርት ቤት ማለት የኔ አባት... ባዶ ሳሉ ምሉዕ የሚሆኑባት ሥፍራ ነች።

ስለዚህ አባቴ... ቢቻሎ እርሶም ሰንበት ተማሪ ይሁኑ፤ አባል ሆነው ይቀላቀሉን፤ ካልተቻሎም አባል የሚሆኑትን አይከልክሉ። ቢቻልዎት ሰንበት ትምህርት ቤትን ከልቦ ይደግፉ፤ ባለዎት ነገር ሁሉ ያበርቱ። ካልቻሉም አደራ አገልግሎቱን ከሚያደናቅፉት ፣ አባላትን ከሚያንገላቱት ጎን አይሁኑ። ቢቻልዎት ስለሰንበት ትምህርት ቤት መልካምነት ያውሩ፤ ባይቻልዎትም ዝም ይበሉ እንጂ ልጆችዎን አይሙ።

ቢቻልዎት በጸሎትዎ ሰንበት ትምህርት ቤትን ያስቡ፤ ባይቻልዎትም ቢያንስ አይርገሙ።

(በዲ/ን ሕሊና በለጠ)